# «ወገብን የሚያጎብጡ መርሃ ግበሮችን በማሳካት አንገታችንን ቀና እናደርጋለን»!

(ታላቁ መሪ መለስ ዜናዊ የካቲት 22/2002 ዓ.ም)

ከታጋይ ሓዱሽ ካሱ

የተፈጥሮ ሕግ ነው እና! ጊዜ ወደፊት እንጂ ወደ ኋላ መመለስ የሚችል ኃይል የለም፡፡ ማይክሮ ሴከንዶች-ሴከንዶችን፣ ሴከንዶች-ደቂቃዎችን፣ ደቂቃዎች-ሰአታትን፣ ሰዓታት-ቀናትን፣ ቀናት-ሳምንታትን እየወለዱ ወደፊት ይጓዛሉ፡፡ 52 ሳምንታት ደግሞ ድፍን አንድ አመታትን ያስቆጥራሉ፡፡

በኢትዮጵያ ብሄር-ብሄረሰቦችና ህዝቦች ልብ ውስጥ ዘላለማዊ ሃውልቱን በመልካም ተግባሩ ተክሎ ያለፈው ታላቁ መሪ ታጋይ መለስ ዜናዊም ማደረግ የሚችለውን ሁሉ አድርጎ ክቡር መስዋትነት ከፍሎ፣ ይህችን ዓለም ከተሰናበተ በወርሃ ነሐሴ አጋማሽ ድፍን አንድ አመት ሞላው፡፡

በአራቱም የአገሪቱ አቅጣጫ ያሉት የኢትዮጵያ ብሄር-ብሄረሰቦችና ህዝቦችም የመለስ ዜናዊ ፋውንዴሽን የአመራር ቦርድ **«ቃልህም ይጠበቃል!» «ወደላቀ ደረጃ ለማድረስም ቃላችንን አድሰናል»!!** በሚል መሪ ቃል ከሃምሌ 15-ነሃሴ 15/2005 ዓ.ም ባሉት ቀናት ለማከናወን ያቀዷቸውን ተግባራት በእምነት ተቀብለው፣ በዋናነት ምድሪቱን አረንጓዴ ለማልበስ ከ6 ቢሊዬን በላይ ችግኞች ሲተክሉ ከርመዋል፡፡

የኢትዮጵያ ብሄሮች-ብሄረሰቦችና ህዝቦች ከአንድ አመት በፊት ማለትም ነሀሴ 14/2004 ዓ.ም ውድቅት ሌሊት አካባቢ ከምሽቱ 5፡40 ሰዓት ላይ ውድ ልጃቸው ታላቁ መሪ መለስ ዜናዊ

መነጠቃቸውን ካወቁበት ሰዓት ጀምሮ <u>«ቃልህን እንጠብቃለ!» የጀመርከውን ሁሉ ዳር ላይ እናደርሳለን»!!</u> በማለት የገቡት ቃል <u>«ዘመቻ መለስ ለአረንጓዴ ልማት የሚል»</u> መሪ ቃል አንግበው እና በሰራዊት መልክ ተደራጅተው ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡ የውድ ልጃቸው የታጋይ መለስ ዜናዊ የሰማዕት መታሰቢያ አንደኛ አመትም በአንድ ወር የሚከናወኑ የተለያዩ ተግባራትን እውን በማድረግ ቃላቸውን አድሰዋል፡፡

የኢትዮጵያ ብሄር-ብሄረሰቦችና ህዝቦች ቃላቸውን ጠብቀዋል፡፡ አሁንም ቃላቸውን አድሰዋል ሲባል መገለጫው ምንድን ነው? የሚል ጥያቄ ቢነሳ ተገቢነት አለው፡፡እውነታውም የኢትዮጵያ ህዝብና የኢፌዴሪ መንግስት እጅ ለእጅ ተያይዘው እያከናወኗቸው ባሉት ዘርፈ ብዙ ተግባሮችና እያስመዘገቧቸው ባሉት ውጤቶች ማሳየት ይቻላል፡፡ ለዚህም የሚከተሉትን ዋነኛ ጉዳዮች በማንሳት ጉዳዩን መዳሰስ ይቻላል፡፡

ታላቁ መሪ ታጋይ መለስ ዜናዊ በህይወት እያለ በኢትዮጵያ ልማት ሲባል ምን ማለት ነው ተብሎ ሲጠየቅ ልማት ማለት በዋነኛነት የሰው ሀብት ልማት ነው፡፡ ይህም በአጠቃላይ ምላዓተ ህዝቡ አስተሳሰቡን ቀይሮ የድህነት ተራራን በእውቀት ንዶ ወደ ብልፅግና ተሸጋግሮ ማየት ነው፡፡ በገጠር ልማት ሲባልም አርሶ አደሩና አርብቶ አደሩ ከኋላ ቀር አስተሳሰብና የአኗኗር ዘይቤ ተላቆ ዘመናዊ ቴክኖሎጅ ታጥቆ ምርትና ምርታማነትን አሳድጎ ኑሮው ሲሻሻል ነው፡፡ በከተማ ደግሞ ዜጎች በዋነኛነት የድህነት መፍቻ ቁልፍ በሆኑት በጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ተደራጅተው ራሳቸውንና አገራቸውን መጥቀም የሚችሉበት ደረጃ ሲደርሱ ነው ብሎ ነበር፡፡

ታዲያ ኢትዮጵያውያን ይህንኑ የታላቁ መሪ ታጋይ መለስ ዜናዊ ቃል አልጠበቁትም ወይ?! ቢባል መልሱ ጠብቀውታል ነው፡፡ እንዴት? ቢባል በገጠር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በሰራዊት መልክ ተደራጅተው የግብርና ምርታችንን በመስኖ ስራዎች ጭምር እየታገዙ የተለያዩ የምርት ዓይነቶች በሄክታር በአማካኝ የነፍስ ወከፍ ምርት ወደ 20 ኩንታል በማድረስ በአምስት አመቱ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ማብቂያ ላይ እንደ ሀገር በዓመት ከ400 ሚሊዮን

ኩንታል በላይ የምናመርትበትና በምግብ ራሳችንን የምንችልበት ሁኔታ ላይ ለመድረስ ጥረታቸውን አጠናክረው ቀጥለውበታል፡፡

በዋነኛነት ይህንን ለማሳካትም በተፈጥሮ ሀብት መስክ 5,940,000 ሄክታር የተፋሰስ ስራ ተሰርቷል፡፡ በ2004/2005 የምርት ወቅትም ከ17 ሚሊዮን በላይ ህዝብ ተሳትፎ፣ በአምስት አመቱ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ መጨረሻ ይገኛል ተብሎ ይጠበቅ የነበረው ውጤት፣ ከወዲሁ ማለትም 13,720 ሚሊዮን ሄክታር መሬት እንዲያገግም በማድረግ ዕቅዱ ተሳክቷል፡፡ በመሆኑም ከ200 ዓመታት በላይ በአፈር መሸርሸርና ደን ምንጠራ እርቃናቸውን ቀርተው የነበሩት ተራሮች በደን ተሸፍነው ልምላሜ ተላብሰዋል፡፡ ወደ ሶስት በመቶ ወርዶ የነበረው የአገሪቱ የደን ሽፋንም ወደ 11 በመቶ ከፍ ብሏል፡፡

ይህም በዋነኛነት በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ያለው 1.8 ከመቶ የአየር ልቀት በ2023 ዓ.ም ወደ 1.1 በመቶ ዝቅ ለማድረግ የታየዘው እቅድ እንደሚሳካ አመላካች መሆኑን ባለሙያዎች በመግለጽ ላይ ይገኛሉ፡፡

በአጠቃላይ በአየር ብክለት እየተጠቃች ያለችው ዓለም ዳግም ህይወት ዘርታ ጥቁር፣ ቢጫ፣ ነጭና ቀይ ቀለም ያላቸው የዓለም ህዝቦች ንፁህ አየር እየተነፈሱ በሰላም፣ በመከባበር፣ በመተሳሰበና በፍቅር ይኖሩ ዘንድ ታላቁ መሪ መለሰ ዜናዊ ቀምሮ፣ ለዓለም ያበረከተው እና ተግባራዊ እንዲሆን ሽንጡን ገትሮ በተለያዩ የዓለም አደባባዮች የተዋደቀለት <u>«የአረንጓዴ ልማት ስትራቴጂ»</u> ስኬታማነት የሚያሳየው ነው፡፡

የኢትዮጵያ ብሄር-ብሄረሰቦችና ህዝቦች በኢህአዴግ እየተመሩ በተፈጥሮ ሃብት እንክብካቤ ያስመዘገቡት ውጤት፣ ታላቁ መሪ ታጋይ መለስ ዜናዊ የቀመረው <u>«የማስፋት ስትራቴጅ»</u> ዕውን ለማድረግም የሰራዊት አደረጃጀታቸውን ወደ አራት ግንባሮች በማዞር ማለትም የሰብል ምርት ማሳደግን ጨምሮ በሌሎች የግብርና መስኮች፣ በጤና፣ በትምህርት፣ እንዲሁም የመልካም

አስተዳደር ችግሮችን ከመሰረቱ ለመፍታት ከኢፌዲሪ መንግስት ጋር እጅ ለእጅ ተያይዞው ደፋ ቀና በማለት ላይ ናቸው፡፡

በከተማ ያሉት በዝቅተኛ ኑሮ የሚኖሩ እንዲሁም ከተለያዩ የትምህርት ተቋማት በሰርቲፊኬት፣ በቲቪቲ፣ ዲፕሎማና ድግሪ የተመረቁ ወጣት ምሁራንም «**ሥራን የመፀየፍ ኋላቀር አስተሳሰብ ሰብረውና እንደየዝንባሌያቸው ተደራጅተው**» በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛሉ፡፡ በመሆኑም በ2005 በጀት ዓመት ብቻ በኮንስትራክሽን፣ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች እንዲሁም ሜጋ ፕሮጀክቶች በመሰማራታቸው 2,221,674 ዜጎች የስራ ዕድል አግኝተዋል፡፡ ይህም ታላቁ መሪ ታጋይ መለስ ዜናዊ አምርሮ የሚጠላውን ድህነት በመቀነስና ስራ አጥነትን በማስወገድ ሂደት የራሱን አስተዋፅኦ አበርክቷል፡፡

በታላቁ መሪ መለሰ ዜናዊ መሪነት በጠንካራ መሰረት ተገንብቶ አገርና ህዝብ እየመራ ያለው ኢህአዴግም የታላቁን መሪ ቃል ጠብቆ በመራመድ ላይ ነው፡፡ ኢህአዴግና ኢህአዴግን ያዋቀሩት አራቱ ብሄራዊ ድርጅቶችም ታላቁ መሪ ከተሰዋበት ዕለት ጀምረው ዴሞክራሲያዊና ልማታዊ መስመራቸውን ይበልጥ አጠናክረው ቀጥለዋል፡፡ ጉባኤዎቻቸውም ዴሞክራሲያዊ ባህሪያቸውን ጠብቀው በስኬት አጠናቅቀዋል፡፡

ታላቁ መሪ ታጋይ መለስ ዜናዊ ለመጀመሪያ ጊዜ በአካል ባልተገኘበት ዘጠነኛ ጉባኤውን ያካሄደውና ከ 6 ሚሊዮን በላይ አባላትን ያፈራው ኢህአዴግም ጉባኤውን በድል አጠናቋል፡፡ በጉባኤውም በዋነኛነት የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅዱ የሁለት ዓመት ተኩል አፈፃፀም ተገምግሟል፡፡ በመጨረሻም ባለፉት ዓመታት የተመዘገበውን ዘርፈ ብዙ ውጤት ይበልጥ ለማጠናከር፣ በአፈፃፀም ክፍተትና ድክመት የታየበትን ደግሞ ለማሻሻል የሚያስችሉ አቅጣጫዎችን ነድፎ ቀንና ሌሊት በመረባረብ ላይ ይገኛል፡፡ በተለይ በ2004/2005 የምርት ወቅት የግብርና አፈፃፀም ከእቅድ በታች የሆነበት ምክንያት አንጥሮ ለይቷል፡፡ መፍትሄውም አስቀምጧል፡፡

በ2005/2006 የምርት ዘመን ከፍተኛ የምርት እድገት ለማስመዝገብም ኢ.ህአዴግ የአመራር ሚናው በመጫወት ላይ ይገኛል፡፡

በኢ.ህአዴግ የሚመራው የኢ.ፌዴሪ መንግስት ከታላቁ መሪ መስዋትነት ማግስት ጀምሮ ታላቁ መሪ በህይወት እያለ ስምምነት የተደረሰበትን የመተካካት መርህ መሰረት በማድረግም ሰላማዊ የስልጣን ሽግግር በማድረግ ድፍን ዓለምን ያሰደነቀ፣ በአንፃሩ ኢ.ህአዴግ እንዲከፋፈል ኢ.ትዮጵያም እንድትበታተን በጠራራ ፀሀይ የሚቃዡት የውስጥና የውጭ ፀረ-ሰላም ኃይሎችን ደግሞ አንገት ያስደፋ ተግባር ፈፅሟል፡፡ ይህም የኢ.ፌዴሪ መንግስት በጠንካራ አለት የተመሰረተ ውስጣዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነቱ እንደ ብረት የጠነከረ መሆኑን በተግባር ያሳየበት ታለቅ ስኬት ነው፡፡

የኢ.ፌዴሪ መንግስት ታላቁ መሪ ታጋይ መለሰ ዜናዊ በህይወት እያለ የጀመራቸው ዘረፈ ብዙ ተግባራት፣ በተለይ ታላቁ መሪ ቢሸፍቱ የሚገኘው የብረታብረት ኢንዱስትሪ የካቲት 22/2002 ዓ.ም በጎበኘበት ወቅት «በጣም ተስፋ ሰጭ ተቋም ነው!!» **«ወገብን የሚያጎብጡ መርሃ-ግብሮችን በማሳካት አንገታችንን ቀና እናደርጋለን»**፡፡ ያለውን አባባል አንግቦ በሰላም፣ በዴሞክራሲ፣ በመልካም አስተዳደርና በልማት ዙሪያ ሰፋፊ ተግባራት በማከናወን፣ ወዳጆች በልበ ሙሉነት፣ ጠላቶች ደግሞ ሐቁን እሬት እሬት እያላቸውም ቢሆን ሳይወዱ ተገደው ምስክርነት የሚሰጡት ተጨባጭ ድሎችን በማስመዝገብ ላይ ይገኛል፡፡

ይኸውም የኢ.ፌዴሪ መንግስት የታላቁ የኢ.ትዮጵያ የህዳሴ ግድብን ጨምሮ በእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅዱ የተካተቱት የመሰረተ ልማትና የማህበራዊ ልማት ወገብ የሚያጎብጡና እልህ አስጨራሽ ተግባራት ሳይስተጓጎሉ ግባቸውን እንዲመቱ አስፈላጊውን ሁሉ አድርጓል፡፡ የኢ.ትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታም እስከ ሰኔ 2005 ዓ.ም ድረስ 26 በመቶ ደርሷል፡፡ የአስር /10/

የስኳር ፋብሪካ ፕሮጀክቶች ስራም ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡ የባቡር መንገዱ ዝርጋታ፣ የመንገድ ግንባታ፣ የቴሌኮምና፣ የኤሌክትሪፊኬሽን ወዘተ መርሃ ግብሮችም ተጠናክረው ቀጥሏል፡፡

በመሆኑም እስከ አሁን ድረስ 52 ሺህ ኪ.ሜትር አገር አቋራጭ መንገዶች ተገንብተዋል፡፡ በእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ ማብቂያም 80 ሺህ ኪ/ሜትር ለማድረስ ስራው ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡ የኤሌክትሪፊኬሽን ስራም 51% ደርሷል፡፡ በ2007 ዓ.ም ሽፋኑ 75% ለማድረስም የተለያዩ ተግባራት በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡ በአጠቃላይ ከሃይድሮ ፣ ከፀሐይ፣ ከጂኦ-ተርሚናል ከንፋስ ሃይል 11 ሺህ ሜጋ ዋት ለማድረስ መጠነ ሰፊ ስራዎች በመሰራት ላይ ይገኛሉ፡፡ የቴሌኮም ስራውም ተስፋፍቷል፡፡ በ2004/2005 የሞባይ ቴሌፎን ተጠቃሚ ቁጥር 22.4 ሚሊዮን ደርሷል፡፡ በ2007 ዓ.ም ደግሞ ቁጥሩ 40 ሚሊዮን ለማድረስ ጥረቱ ቀጥሏል፡፡ የአ/አ ባቡር ዝርጋታም 43%፣ ሰበታ-አ/አበባ 22% እንዲሁም መኤሶ-ድሬዳዋ 20% ደርሷል፡፡ ይህም በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ለማከናወን የተያዘው 2,395 ኪ/ሜትር የባቡር ሃዲድ ዝርጋታ እንደሚሳካ አመላካች መሆኑን በዘርፉ የተሰማሩ ባለሙያዎች ያረጋግጣሉ፡፡

በማህበራዊ ልማት ዘርፍ ረገድም የሚሊኒዬም የልማት ግቦች ከሚያሳኩ አገራት አንዷ ኢትዮጵያ መሆንዋ ዓለም አቀፍ ማህበረሰብ ደግሞ ደጋግሞ ምስክርነቱን ሰጥቷል፡፡ ይህም የአገሪቱ የጤና ሽፋን 93 በመቶ፣ የውሃ ሽፋን 61.3 በመቶ ደርሷል፡፡ በትምህርት ረገድም የአንደኛ ደረጃ ጥቅል ቅበላ ምጣኔ 96 በመቶ፣ ሁለተኛ ደረጃ 39 በመቶ ደርሷል፡፡ በ1983 ሁለት ዩኒቨርሲቲዎች የነበሯት ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት የ31 የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች ባለቤት ሆናለች፡፡ ከእነዚህ የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎችም በ2005 ዓ.ም ብቻ 67,595 ተማሪዎች ተመርቋል፡፡ በ2006 ዓ.ም ደግሞ ከ100,000 በላይ ተማሪዎች ለመቀበል በመሰራት ላይ የገኛል፡፡ <u>በአጠቃላይ ኢትዮጵያ ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት እያስመዘገቡ ካሉት 10 የዓለም አገሮች አንዷ ሆናለች፡፡</u>

የኢ.ፌዴሪ መንግስት ታላቁ መሪ የቀየሰውን **«የሰጥቶ-መቀበል መርህ እንዲሁም ኢንቨስትመንትና ንግድን መሳብ»** ማዕከሉ ያደረገውን የኢ.ፌዲሪ የደህንነትና የውጭ ጉዳይ ፖሊሲም ተጨባጭ ውጤት በማስመዝገብ ላይ ነው፡፡

ይþውም ኢትዮጵያ የአፍሪካ ህብረት የአመቱ ሊቀመንበር ሆና ተመርጣለች፡፡ በ22 ዓመታት ጊዜ ውስጥ ታላቁ መሪ ታጋይ መለስ ዜናዊ ለመጀመሪያ ጊዜ በአካል ያልተገኘበት የአፍሪካ ህብረት ስብሰባ እንዲሁም የቀድሞ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት (OAU)፣ የአሁኑ የአፍሪካ ህብረት (AU) 50ኛ ዓመት የወርቅ ኢዮብልዩ በዓልም በድምቀት አክብራለች፡፡ በዓሉ የኢትዮጵያ ሚና ጎልቶ የታየበትና ገፅትዋም በአዎንታ እንዲታይ ያደረገ ነው፡፡ ኢትዮጵያ የአነዋ ፎረምን ጨምሮ በርካታ ዓለም አቀፋዊና አህጉራዊ መድረኮችን አስተናግዳለች፡፡ ኢትዮጵያ እያስመዘገበች ባለው ተከታታይ እድገትም ገፅታዋ በአዎንታ መልክ እየተለወጠ በመሄዱ የኮንፈረንስ ቱሪዝም ማዕከል እየሆነች ነው፡፡ የውጭ ኢንቨስትመንት በመሳብ ረገድ እንዲሁም ከምዕራቡም ሆነ ከምስራቁም ዓለም ብድርና እርዳታ የምታገኝበት ዕድልም እየሰፋ መጥቷል፡፡

ኢትዮጵያ አሁንም የአፍሪካ ቃል አቀባይ ሆና ቀጥላለች፡፡ የአፍሪካ ድምፅ ወክላም በቡድን 20፣ በቡድን 8፣ በBRICS ፎረም ወዘተ... በመሳተፍ ላይ ነች፡፡ በአጭሩ የኢትዮጵያ ዓለም አቀፋዊ ተቀባይነትዋና ተደማጭነቷ ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡

ታዲያ ከዚህ በላይ ቃል መጠበቅ ምን አለ? ቢባል ከተመዘገበው ውጤት በላይ ሌላ ከፍተኛ ውጤት ለማስመዝገብ ቀንና ሌሊት ሊሰራ ይገተባል ካልተባለ በስተቀር፣ የኢትዮጵያ ብሄር-ብሄረሰቦችና ህዝቦች ቃል መጠበቁ፣ ምስክሩ ተግባር ስለሆነ የታላቁ መሪ አደራ ተጠብቆ ተግባራዊ አድርጓል ቢባል ሐቁን መናገር እንጂ ማጋነን አይሆንም፡፡

ሆኖም የኢትዮጵያ ብሄር-ብሄረሰቦችና ህዝቦች እንዲሁም የኢፌዴሪ መንግስት፣ በኢህአዴግ መሪነት በአንድ ግንባር ተሰባስበው እና የታላቁ መሪ ታጋይ መለስ ዜናዊ አደራ ተጠብቀው ይህንን ሁሉ የሚዳስስ ድል ያስመዘገቡት ሁሉም ነገር አልጋ በአልጋ በሆነ አግባብ አልነበረም፡፡

ይልቁንም በርካታ ፈታኝና ውስብስብ ሁኔታዎች በማለፍ ነበር፡፡ ይኸውም ታላቁ መሪ ታጋይ መለስ ዜናዊ አምርሮ የሚጠላወና ከወጣትነት ጊዜው ጀምሮ እስከ ህልፈተ ህይወቱ ድረስ የታገለውን፣ የድህነት ዘበኛ የሆነው ኪራይ ሰብሳቢነትንና ሙስናን እንዲሁም አክራሪነትንና ሽብርተኝነትን በመታገል ነበር፡፡ በዋነኛነት ታላቁ መሪ በህይወት እያለ «የመንግስት ሌቦች» እና አየር በአየር መክበር የለመዱ ኪራይ ሰብሳቢዎችን በጥናት ተመስርቶ የጀመረው ትግል፣ በተተኪ ወጣት አዲስ አመራር የተገነባው የኢፌዴሪ መንግስትም፣ የታላቁ መሪ አደራ ተቀብሎ በ2005 ዓ.ም በሙስና የተጨማለቁ ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናትንና ተባባሪዎቻቸውን መንጥሯቸዋል፡፡ አሁንም የኢትዮጵያን ህዝቦች ከጎኑ አሰልፎ ትግሉን ከዳር እስከ ዳር ተቀጣጥሎ እንዲቀጥል ተገቢው አመራር በመሰጠት ላይ ይገኛል፡፡

ከዚህ ሌላ በሀይማኖት ሽፋን ድብቅ ዓላማቸውን ለማራመድ አክራሪ-አሸባሪዎች ከውስጥና ከውጭ ፀረ-ህዝብና ፀረ-ልማት የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር ጋብቻ ፈፅመው ያደረጉትን እንቅሰቃሴ የኢትዮጵያ ህዝቦች ከኢፌዲሪ መንግስት ጎን ተሰልፎ በጋራ ባደረጉት ትብብር መክተውታል፡፡ የጽንፈኛው አክራሪና አሸባሪ ቀንደኛ መሪዎችም በቁጥጥር ስር ውለው ጉዳያቸው በህግ ፊት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ትግሉ ተጠናክሮ እንዲቀጥልም የኢፌዲሪ መንግስት የኢትዮጵያ ብሄር-ብሄረሰቦችና ህዝቦች ከጎኑ አሰልፎ ሰፊ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የኢፌዴሪ መንግስት የኢትዮጵያ ህዝቦችን ከጎኑ አሰልፎ ሙሰኝነትን፣ አሸባሪነትን እንደተዋጋው ሁሉ የኢትዮጵያ ታላቁ የህዳሴ ግድብ ግንባታ ለአንዲት ሴኮንድም ቢሆን ሳይስተጓጎል መቀጠሉ ያንገበገባቸው፣ በዋነኛነት ውስጣዊ የፖለቲካ ችግራቸውን ለመሸፋፈን

የተሯሯጡት አንዳንድ የግብፅ የፖለቲካ ኃይሎች  እንዲሁም በገንዘብ የገዟቸው ኢትዮጵያዊ ደም ያላቸው አገር የከዱ ጸረ-ልማት ፖለቲከኞች ነን ባዮች፣ ኢትዮጵያ ውስጥ የአረቡ ዓለም አይነት አመፅ ቀስቅሰን የኢትዮጵያ ብሄር-ብሄረሰቦችና ህዝቦችን እናተራምሳለን በማለት ግራና ቀኝ ያራገቡትን አሉባልታ በፅናትና በትግዕስት መክቷል፡፡ ይህም የኢፌዴሪ መንግስት ምን ያህል በበሳል አመራር የሚመራ መሆኑ ለወዳጅም ለጠላትም አሳይቷል፡፡

**አዎን ያቺ ዕለት**!! ማለትም ነሐሴ 14/2004 ዓ.ም ውድቅት ሌሊት እንዲሁም ነሀሴ 15/2004 ዓ.ም የኢትዮጵያ ብሄር-ብሄረሰቦችና ህዝቦች እና የኢፌዴሪ መንግስት እንዲሁም በአራቱም የዓለም ማዕዘናት ላሉት ግፉዓን ህዝቦች መራራ ናት፡፡ ሆኖም ማስቀረት የማይቻል እየመረረህ የምትውጠው በጣም አሳዛኝ እውነታ የተከሰተባት ዕለት ስለሆነች፣ ተወደደም-ተጠላም መዘከሯና መታሰቧ የማይቀር ዕዳ ነው፡፡

**ሆኖም ያቺ ዕለት**!! በ2005 ዓ.ም የምንዘክራት እንዳለፈው ዓመት በሃዘንና በለቅሶ አይደለም፡፡ ሊሆንም አይገባም፡፡ ይልቁንም የኢፌዴሪ መንግስት፣ የኢትዮጵያ ብሄር-ብሄረሰቦች ህዝቦችን ከጎኑ አሰልፎ በቀሪ ሁለት የእድገትና የትራንስፎርሜሽን አመታት፣ ከፍተኛው የእድገት አማራጭ /High case scenario/ ለማሳካት፣ የጀመረውን መጠነ ሰፊ ርብርብ ለማሳካት እያንዳንዱ ሰላም፣ ዲሞክራሲ፣ መልካም አስተዳደር፣ ልማት ወዳድ ኢትዮጵያ በቁርጠኝነት ተነሳስቶና ቃሉን አድሶ ሆ ብሎ የመነሳቱ ጉዳይ ቅድሚያ የሚሰጠው ነው፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ «**በዛች ዕለት**»!! የኢትዮጵያ ብሄር-ብሄረሰቦችና ህዝቦች እንዲሁም የዓለም ግፉአን ህዝቦችን ለመታደግ ሲል እንደሻማ የቀለጠው ታላቁ መሪ ለመዘከር የተቋቋመው እና ባለቤቶቹ የኢትዮጵያ ብሄር-ብሄረሰቦችና ህዝቦች የሆኑት የመለስ ዜናዊ ፋውንዴሽን በጉልበታችን፣ በእውቀታችን፣ ንብረታችንና ገንዘባችን ለማጠናከር የቻልነው ሁሉ ለማድረግ የምንነሳበት ነው፡፡

በአጭሩ **«በዛች ዕለት»!!** ታላቁ መሪ መለሰ ዜናዊ በህይወት እያለ የጀመራቸው **«ወገብን የሚያጎብጡ መርሃ-ግብሮች በማሳካት አንገታችንን ቀና እናደርጋለን!!»** ብቻ ሳይሆን አገራችን ኢትዮጵያ በራስዋ የአቆጣጠር ዘመን ማለትም 2015 መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ ለማሰለፍ የተያዘው ግብ እንዲሁም ከፍተኛ እድገት ካስመዘገቡት አገራት ደግሞ ከ30 እና 40 ዓመታት በኋላ እንዴት መድረስ እንደሚቻል፣ ታላቁ መሪ መለስ ዜናዊ ቀምሮ የተወልንን የህዳሴ መስመሮች ሳይከለሱና ሳይበረዙ ለማሳካት ከምን ጊዜም በላይ በእልህ የምንነሳበት ጊዜ አሁን መሆኑን አውቀን የምንረባረብበት ነው፡፡ **«በዛች ዕለት»!!** ዳግም ቃላችን ስናድስ የታላቁ መሪ ታጋይ መለስ ዜናዊ ህያውነት ይበልጥ በማጠናከር መጪው ጊዜ በስኬት የምንረማመድበት አዲስ ዓመት እንደሚሆን አያጠራጥርም፡፡

**ቸር ይግጠመን!!**